ምዕራፍ አምስት

በአመራሩ ሥር አንድ የሆኑ አገሮች

1. ሱልጣን ኑረዲን ከሞተ በኋላ የሙስሊሙን ዓለም በአንድ ማንዲራ ሥር አንድ የማድረጉ ታሪካዊ ኃላፊነትና ዕድል በዚህ ጀግና ሻ ሻ ላይ አረፈ። በርግጥም በነበረው ወታደራዊ ብቃት፣ ፖለቲካዊ ብስለትና የጦር ስልት ሁሉንም አገሮች አንድ በአንድ በአመራሩ ሥር ማምጣት ችሎ ነበር። የመን አርስ በርሳቸው በሚዋጉ የተለያዩ ሁድኖች ትታመስ ነበር። በማያቋርጥ ሽኩቻ በተጠመዱት ሁድኖች ምክንያት ተጠባነሳ ነበር። ሰንዓ ላይ ሐምዳናይቶች፣ ዙበይድ ላይ ነጃይቶች ለሥልጣን ይታገሉ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ራሱን የሚጠበቀው መህዲ[5] አድርጎ የሸመና የሐሰት ፕሮፓጋንዳ የሚረጭ፣ አገሪቱ ውስጥ ብጥብጥ፣ የእርስ በርስ ጦርነትና ሥርዓት አልበኝነትን በማንገስ ለደም መፋሰስ ምክንያት የሆነ ግለሰብ ነበር። በሙስሊሞች የርስ በርስ መጋደልና መጠላለፍ ሲታመም የኖረው ሰላሑዲን ለዚህ ሁሉ ክንቱ ግዙፍነትና ሥርዓት አልባነት መቋጫ እንዲያበጅለት በማሰብ ወንድሙን ጡረንሻህን ወደ የመን ላከው። ወንድሙም የመን በሰላሑዲን አመራር ሥር ከግብፅና ሶሪያ ጋር እንድትቀላቀል የሚድረጉን ተልዕኮ በተሳካ ሁኔታ አከናወነው።

2 ጡረንሻህ ሠራዊቱን ይዞ የአሳይን መንዝ ተከትሎ ታስ ከተማ እስኪደርስ ድረስ ተጓዘ። ቀጥሎ ከቀይ ባህር ዳርቻ እስኪደርስ ድረስ በየበስ ተጓዘ። ከዚያም ቀይ ባህርን በማቋረጥ ወደ ጅዳና ወደ የመን ተጓዘ። የዙበይድን ግዛትና ሌሎች ጥቂት የመከላከያ ምሽጎችን ተቆጣጠረ። አንዳንድ ታሪክ ሊቀራሞች ከሰማንያ በላይ ምሽጎችንና ከተማዎችን መቆጣጠር ችሎ እንደነበር ዕረዋል። የመናዊያን የናርነበትን ሥርዓት አልባ ሕይወት ያስተርልናል ብለው ስላሰቡ የጡረንሻህን መምጣት በታላቅ ደስታ የተቀበሉት ይመስላል። የተወሰኑ የመናዊያን ያለምንም ደም መፋሰስ አገሪን እንዲቆጣጠር ረዱት።

መህዲ አል-ሙንተዘር በመጨረሻው ዘመን ወደ መሬት ይመጣል ተብሎ የሚጠበቅ፣ በፍትህ የሚያስተዳደር ሰዎችን ወደ ቅኑ ጎዳና የሚመራ፣ ቂን እና ቀጥተኛ የሆነ መሪ ነው። (ተርጓሚ)

ህዝቡን ከጠላት ጥቃት ለመከላከል አስበው የገነቧቸውን በርካታ ግዙፍ ግንቦች የበሮቻቸውን ቁልፍ እያመጡ አስረከቡት። ከሥርዓት አልበኝነት ወጥተው የተረጋጋ ሕይወት ለመምራት አልመው ነበርና ይህን አደረጉ። ጡረንሻህ የመንን ሙሉ ለሙሉ በእጁ ማስገባቱን ካረጋገጠ በኃ ለአመራሩ ተስማሚ ማዕከላዊ ቦታ ለመምረጥ ከአማካሪዎቹ ጋር ተቀመጠ። የተዕዝ ከተማን ማዕከላዊ ቢሮው ለማድረግ ወሰነ።

3. ሰላሑዲን ወንድሙን ጡረንሻህን የየመን አስተዳዳሪ አድርጎ ሾመው። ቀጥሎ ሌላውን ወንድሙን ጠሽታኪን ኢብን አዩብን ሾመ። ጠሽታኪን እ.ሒ.አ በ593 እስኪሞት ድረስ የመንን ገዛ። በአጠቃላይ የአዩብ ቤተሰቦች የመንን እ.ሒ.አ ከ 569—652 ማለትም ከ80 ዓመታት ሰላይ መምራት ችለው ነበር።

4. የመን በተያዘችበት በዚያው ዓመት (እ.ሒ.አ 569) ሰላሑዲን በበኩሉ በርካህን፣ ትሪፖሊንና የቱኒዚያን ቃቢስ ድረስ ያለውን ምስራቃዊ ክፍል ተቆጣጠረ።

5. እ.ሒ.አ በ579 ሰላሑዲን የሙስሊሙን ዓለም አምባሳደሮች ደማስቆ ውስጥ ወዳዘጋጀው ኢስላማዊ ኮንፈረንስ ጋበዘ። ወንድሙን ማሊክ ዓዲልንም ኮንፈረንሱ ላይ እንዲገኝ ጥሪ አድርጎለት ነበር። ጥሪውን አክብረው ኮንፈረንሱ ላይ ከተገኙት መካከል፡- ታላቁ ሸህ ሶድረ-ዲን፣ ሺሐቡ-ዲን በሺር፣ የአባሲዶች ኸሊፋ የናስር ሊዲኒላህ ልዑክ፣ አል-ቃዲ ሙሒዩ-ዲን አሸህራዙሪ ፣ በሐአ-ዲን ኢብን ሸዳድ፣ የሞሱሉ ገዥ አምባሳደርና የአልጀዚራህ ገዥ አምባሳደር የነበረው ሙዓዙ-ዲን ኢንጃር እንዲሁም ሌሎች በርካታ ሰዎች ይገኙበታል። ሰላሑዲን በሙስሊሙ ዓለም መሪዎች መካከል የነበሩትን ሁሉንም ዓይነት አለመግባባቶችና ግጭቶች ለማስወገድና በምትካቸው ወንድማማችነትንና ስምምነትን ለመፍጠር ብርቱ ጥረት አደረገ። ከሞሱሉ አምባሳደር በስተቀር ሁሉም አምባሳደሮች በአንድነቱ ተስማሙ። ሰላሑዲንን በፅኑ የተቃወመና አለመስማማቱን የገለፀ ብቸኛ ሰው የሞሱሉ አምባሳደር ነበር።

6. በሙስሊሙ ዓለም የተፈጠረውን አንድነት መቃወሙን የተመለከተው ሰላሑዲን የሞሱሉን ገዥ ከአፈንጋጭነቱ እንዲመለስና

ትክክለኛውን መንገድ እንዲከተል ለማድረግ ኃይል መጠቀም እንዳለበት አመነ። ሰላሑዲን ከተማውን የከበባት ጊዜ የሞሱሉ ገዥ ዒዘ-ዲን ያለማንገራገር እጅ ሰጠ። ኢዘዲን እ.ሒ.አ በ581 የተደረገውንና የሐራን ስምምነት ተብሎ የሚታወቀውን ስምምነት ተቀበለ። ዒዘዲን በስምምነቱ መሠረት ሽሐር ዙር፣ ኦል-ቀራቢሊና፣ ጠፍጃክ የተባሉትን ከተማዎችና በዙሪያቸው የሚገኙትን ወረዳዎችን ለሰላሑዲን አስረከበ። ሰላሑዲን በበኩሉ በጁሙዓ ኹጥባ ላይ ስሙ እንዲጠቀስና በሳንቲሞች ላይ ስሙ እንዲቀረፅ የሚያስገደዱ መስፈርቶችን በማስቀመጥ የሞሱልን ከተማ ለዒዘዲን ተወለት። ከዚህ በተጨማሪ ዒዘዲን የሰላሑዲንን ፖሊሲ የመከተል ግዴታ ተደረገበት።

ኢብን ወሲል "መፍረጅ አል-ኩሩብ ፊ ተዋሪኽ በኒ አዩብ" በሚባለው መፅሐፋቸው ውስጥ የሚከተለውን አስፍረዋል፦ "ከሐራን ስምምነት በኋላ ከሞሱል፣ ከሳንጃር፣ ከአል-ጀዚራህ፣ ከአርቢል፣ ከሐራን፣ ከዲያር በክር እና ሌሎች ቦታዎች የተውጣጡ ወታደሮችን ከስንት ዘመን የእርስ በርስ ሽኩቻ በኋላ በአንድ ባንዲራ ስር ማሰባሰብ ቻለ።"

7. ሰላሑዲን ካከናወናቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ባግዳድ ለሚገኘው የአባሲዶች ኸሊፋ አል-ሙስተዲ መልዕክት መላክ ነበር። የሰላሑዲን ግዛቶች የበላይ አስተዳዳር (ወዚር) የነበረው ቃዲ ፈድል ነበር መልዕክቱን የፃፈው። በመልዕክቱ ውስጥ ሰላሑዲን ከጠላት ጋር ያደረጋቸውን ጦርነቶች፣ ግብፅን፣ የመንንና ሰሜን አፍሪካን መቆጣጠሩን እና በጁሙዓ ኹጥባዎች ላይ የአባሲዶች ኸሊፋ ስም እንዲነሳ ማድረጉን በመጥቀስ የሰላሑዲንን ስኬቶችና የጂሃድ ተግባሮች ገልፆ ነበር። በተጨማሪም የግብፅ፣ የሞሮኮ፣ የየመን፣ የሶሪያ እና ዘግይተው በቁጥጥሩ ሥር የሆኑ ሌሎች አገሮችን የመምራት ሥልጣኑን ለሰላሑዲን እንዲሰጠው ኸሊፋውን ጠይቆ ነበር። ኸሊፋው አል-ሙስተዲ እነሰላሑዲን ለመምራት የጠየቋቸውን አካባቢዎች ለይቶ የሚያረጋግጥ የልዑክ ቡድን በመላክ ፈጣን መልስ ሰጣቸው። እንዲሁም ስጦታዎችንና የክብር ልብሶችን ላከላቸው።

8. ቀደም ብለን እንዳየነው ሰላሑዲን በጣም ብዙ አገሮችን በአንድ ባንዲራ ሥር አሰለፈ። ከራመላህ እስከ አባይ ተፋሰስ ከሰሜን አፍሪካ

እስከ ትሪፖሊ ድረስ ያሉ ከተማዎችን ግዛ፣ ከግብፅ፣ ከሶሪያና ከዓራቅ ለሚናዊ ክፍል በተጨማሪ የመንን፣ ኤደንን፣ የትሪፖሊ የባህር ዳርቻዎችንና እስከ ታቢስ ድረስ የሚገኙትን የቱኒዚያን ክፍሎች ገዛ። በእነዚህ ሁሉ ግዛቶችና ከተማዎች ውስጥ በሚደረገ የጁመዓ ጉጉባዎች በመሉ ስመ ይነሳ ነበር። በአጠቃላይ በግዛቱ ሥር የሚገኙ አገሮች የሚከተሉት ነበሩ፦ ሰሜን ኢራቅ (ኩርድ)፣ ታላቋ ሶሪያ፣ የመን፣ ግብፅ፣ ሞሮኮና የሰሜን አፍሪካ ዳርቻዎች ነበሩ።

የሁሉም አገሮች ህዝቦች በሰላሑዲን ላይ ትልቅ ተስፋ ጥለው ነበር። ለመስለመ ዓለም አንድነትና ዋስትና አድርገው ተመልከተውት ነበር። ከዚህ ጠንካራ አንድነትና ትስስር በኋላ ዕድሜ ልኩን ሲጠብቀው የኖረው ወሳኝ ትግል ጊዜው ደረሰ።

9. በጊዜው ህዝቦች በማይመጥኗቸው መሪዎቻቸው የተሰቃዩበት ጊዜ ነበርና መስለሞች ወደ አንድነት የመምጣታቸውን መልካምነት የሚያወሱ ግጥሞች ይገጠሙ ነበር። ለምሳሌ የኢብን ሲናን ግጥም ይህን ይመስል ነበር፦

ህዝብን የማይመጥኑ
የልዩ አዕምሮ ያላቸው
ገዥዎች በመሆናቸው
ህዝብ ተቸገረ
መልካም መሪ አጥቶ
እጅግ አማረረ
ሳላሃዲን የመጣ 'ለት
በሽታ ታክመ
ተወገደ ብክለት

በሊላ በኩል የመስለመ ዓለም ወደ አንድነት መምጣት በዘፋት ከተሞት የመስተል ወራሪዎች እየሩሳሌምን ነፃ ለማውጣትና የኢስላምን ድል ለማረጋገጥ የሚቻልበት መንገ ይሆናል ብለው

አምነው ነበር። የየሩሳሌም ነፃ መውጣት ደግሞ አጠቃላይ ፍልስጤምን ነፃ የማውጣቱ ትግል የመጀመሪያ እርምጃ ይሆናል። ዲማድ አል. አስበሃኒ ስላሉዲንን በግጥሙ እንዲህ በማለት አወድሶት ነበር፡-

በማሸነፍህ ኢስላም ኮራ
በድልህ ቀኑ በራ
ለዓለም፣ ለዲኑ ብዙ አደረክ
ጥንካሬን፣ ተስፋን አበረከትክ
እንግዲያውስ እየሩሳሌምን በመያዝ
ድልህን ምሉዕ አድርገው
ገስግስ፣ ቀጥል ወደፊት
ኢስላምን ለድል ለማብቃት
ሥርዓቱ አስኪሰልም አትረፍ